★ ዴሞክራሲያ ★

* የኢትዮጵያ ሕዝባዊ አብዮታዊ ፓርቲ ልሳን *

ቅጽ 34 ቁጥር 9 ሐምሌ 2001 ዓ.ም.

# <u>ለመጪው ትውልድ አይለጉት ሐኬት</u>

አንድ ትውልድ÷ የተረከበውን ሀገር የማስረክብ ÷ የቆየለትን የመጠበቅ ብቻ ሳይሆን ተረክቦ የጠበቀውን የሚረከብለት ተረካቢ ትውልድ የማዘጋጀት ኃላፊነት ያለበት መሆኑን አበክሮ ሊገነዘበው ይገባል ። የተረከባትን ሀገር ማስረከብ ሲባል÷የቆዳ ስፋቷ እንደተጠበቀና እንደተከበረ ማቆየቱ ብቻ ሳይሆን ÷ ተረካቢውን ትውልድ በሁለንተናዊው ረድፍ አስተምሮ ÷ አሰልጥኖ ÷ አሳድጎና አዘጋጅቶ የተረካቢ ኃላፊነቱንም ጭምር በብቃት እንዲወጣ ማድረግንም ጭምር የሚጠይቅ ነው ። የአንድ ሀገር አረጋውያን እያለፉ ወጣቱና ጎልማሳው መተካቱ የተፈጥሮ ሕግ በመሆኑ÷ አስረካቢው ለተረካቢው ሊያሳልፍ የሚችለው ÷ የራሱን ኃላፊነት በብቃት ተወጥቶ ሲገኝ እንጅ÷ እንዲያው በደፈናው ባወጣው ያውጣው በሚልና እኔ በበኩሌ የሚገባኝን ሰርቻለሁ ÷ የቀረውን ግን÷ <u>የኋላ ልጅ ይጨነቅበት</u> ከሚል በዘልማድ በተለወሰ ሂደት ከሚመጣ ክስተት ሊሆን አይገባውም። አዲሱ ትውልድ ሀገሩን ለመረከብ ብቃት እንዲኖረው ካስፈለገ÷የሚረከባትን ሀገር÷ ሀገር አድርገው ያቆዩዋትን ጀግኖች ÷ ስመ-ጥር አርበኞች ደራሲያንና ምሁራን ÷ ሊቃውንት በአርዓያነት እንዲመለከታቸውና እንዲያከብራቸው ይገባል ። የቆዩትን ጀግኖች ÷ አርበኞች ሊቃውንትና ጠቢባን እያጠፉ ባዶ የሆነች ሀገር ጥሎ ማለፍ፤ ተተኪውን ትውልድ ብቻ ሳይሆን÷ ሀገሯን ራሷንም ጭምር አጥፍቶ ማጥፋት ይሆናል ። ቢያንስ ከአንድ መቶ ዓመታት ወዲህ ያለውን የሀገራችንን ዕውነታ ስንመለከት ከሞላጎደል የሀገር ተረካቢን ትውልድ ማዘጋጀት ጭራሽ ተረስቶ እንደ ነበር አሁን ያለው የሀገራችን ሁኔታ ያረጋግጣል ። ለሀገር ተቆርቋሪውን ትውልድ ሁሉ እየጨፈጨፉ ተረካቢ ኃይል ይገኛል ብሎ ተስፋ ማድረግ ቀርቶ ÷ ማለምም የሚቻል አይደለም። ተረካቢ ትውልድ ያላገኘች ሀገር÷ ለሚገነጣጥሏት አራዊት እንደምትዳረግ የዛሬይቱን ኢትዮጵያ እንደ ምሳሌ መጥቀስ ተችሏል ። ፋሺስቱ ወራሪ የኢጣሊያ ወታደር ወጣቱንና ምሁሩን በመጨፍብፍ ላይ አተኩሮ የነበረው አለምክንያት አልነበረም።

እንዲያው በደፈናው÷ በወደቀ ግንድ ላይ ምሳር ማብዛት÷ የሞተ ፈረስ እንደመጋለብ አይቆጠር እንጅ÷ ኢትዮጵያ ሀገራችን ተረካቢ ትውልድ እንዳይኖራት በማድረግ ደርግ÷ ከታሪክና ከሕግ ተጠያቂነት ነፃ ሊሆን አይችልም ። መጭው ትውልድ የሀገሩን ታሪክና የወደፊት ዕድል ለመመርመር በሚያደርገው ጥረት÷ ይህን ዕውነታ ፍንትው ብሎ ሊታየው ይችላል ።

***ፀረ ዴሞክራሲ የሆኑ ገዥዎች ሁሉ ፥ የሀገርን ዘላቂ ጠላትና ዘላቂ ወዳጅ የመለየት ፍላጎቱም ይሁን ራዕዩ ስለማይኖራቸው ፥ ለሥልጣናችን አደገኛ ነው ብለው የሚያስቡትን ሁሉ ከማወድም ወደኋላ አይሉም፡፡***

***የስድሳ ስድስቱ የኢትዮጵያ አብዮታዊ ትውልድ በብሔርም ይሁን በሃይማኖት ሳይከፋፈል በአንድ ላይ ተባብሮ የቆመው ለሀገሩና ለዜጎቿ መልካምን በማሰብ ነበር፡፡ ለዚህም አይከፍሉ መሥዋዕት ከፍሏል፡፡ ያ ሁሉ እንደቅጥል የረገፈው ምሁርና ወጣት ለሀገሩ የነበረው ራዕይ በብሩኅ ተስፋ፥በሀገር አንድነትና በሕዝብ እኩልነት ላይ የተመሠረተ ነበር፡፡ታዲያ የደርግ ባለስልጣኖችና ጀሌዎች ይህንን ለኢትዮጵያ ብሩኅ ተስፋ አንግቦ የቆመውን አዲስ ትውልድ እየጨፈጨፉ ፥ ኢትዮጵያን ለመከፋፈልና ለመቆራረስ ዓላማ አድርጎ የተነሳውን ጠባብ ብሔረተኛ ድርጅት ሰተት ብሎ አዲስ አበባ በመግባት ዓላማውን በተግባር እንዲተረጉም ዕድል ሰጡት ፡፡ ወደዱም ጠሉም በተጨባጭ ተበባበሩት፡፡ በአሁን ወቅት አንዳንድ የመረጃ ሰነዶች እንደሚመሰክሩት፥ ሕሊናቸውን በመሸጥ ከወያኔ ጋር ተባብረው የውስጥ መረጃ በማቀበል አሳፋሪ ድርጊት የፈፀሙ የደርግ ባለሥልጣናት ቁጥራቸው ጥቂት አይደለም፡፡ እነኝህ ግለሰቦች ደግሞ ለሀገር የቆመውን ኃይል በማጥፋት ብቻ ሳይወሰኑ፥ ተተኪውን ትውልድም ጭምር እያወደሙ፥ ኢትዮጵያን ለአውዳሚ ተምች አሳልፈው አስረክበዋል፡፡ ይኸም ደግሞ ከጠፉም በኋላ የጥፋታቸው ጠንቅ እንዲቀጥል ሆኗል ፡፡ <u>የኢትዮጵያን ጉዳይ የኋላ ልጅ ይጨነቅበት</u> እንዳይሉ እንኳ ፥ የኋላ ልጅ እንዲተርፍ አላደረጉም ፡፡ መጪው ትውልድ በጠፋበት ኃላፊነት ይሰጠው ቢባል እንኳን፥ የሚለጋለት ሀኬት ሊኖር አይችልም--አልቋልና፡፡ ለአንድ ሀገር ከሚወረሱት ውርሶች መካከል የኋላ ልጅ ይጨነቅበት የሚባለው ነገር፥ ሀገር እንደ ሀገር ለመቀጠል እንዳትችል የሚደረግ ጠላትነት ነው ፡፡በግድ ኢትዮጵያ ሀገራችን የነገን ተረካቢ ትውልድ እንድትፈጥር ዕድል ሊሰጣት ይገባል፡፡***

***ኃላፊነት ተሰምቶት ሀገሩን ለመረከብ ብቃት ያለውን የነገን ተረካቢ ትውልድ ለማሰናዳት ልዩ ልዩ ብሔራዊ ተቋማት እንዲኖሩ የግድ ይላል፡፡ በማንኛው ኅብረተስብ ውስጥ የተቋማቱ መሠረት ቤተሰብ መሆኑ የሚያከራክር አይሆንም ፡፡ "ወላጅ ያቆየው ለልጅ ይተርፈው" እንደሚባለው የወላጆችና የልጆች መኖር ምሶሶውና ማገሩ፥ጣራው መሠረቱም ቤተሰብ ነው፡፡መልካም ቤተሰብ ደግሞ መፈጠሩ ብቻ ሳይሆን ህይወቱም ዋስትና ሊኖረው የሚችለው፥ ሀገር ሲኖር ሲችል ነው፡፡ በዘርና በቋንቋ የተከፋፈለ ሀገር ደግሞ ዋስትና ያለው ጤናማና መልካም ቤተሰብ ማፍራት ቀርቶ የሀገርም ጨገሬታ ቢሆን ሊያቆይ አይችልም ፡፡ ይህ በዛሬይቱ ኢትዮጵያ ዕለት በዕለት የሚታይ ክስተት ሆኗል ፡፡ ሀገርን ከመሠረቱ መነጋግሎ ለማፍለስ ፥ ቤተሰብን ማናጋትና መነቃቀል ፥ የሀገር አጥፊዎች እኩይ ተግባር በመሆኑ ፥ የዛሬዎች የኢትዮጵያ ገዥዎች ያለመታከት የኢትዮጵያን ቤተሰብ አናግተውታል ፡፡ በመሆኑም ፥ የአንድ ሀገር መሠረት የሆነው የቤተሰብ ተቋም ጠፍቷል ማለት ነው ፡፡ ለአንድ ሀገር ኅልውና መሠረት የሆነው የመጀመሪያው ተቋም ቤተሰብ***

እንደመሆኑ÷ ለሀገር የሚጠቅሙ ልዩ ልዩ ተቋማት ለማቋቋም÷ በግድ የተቋማቱ ሁሉ መሠረት ሊሆን የሚችለውን የቤተሰብ ተቋም ማክበርና ማፋፋት አስፈላጊ ነበር። መልካም ቤተሰብ ኖሮ÷ መልካም ትውልድ ካልተፈራ÷ የነገይቱን ኢትዮጵያ ለመረከብ የሚችል ትውልድ ማፍራት የሚቻል አይሆንም ። ምንም እንኳ በዛሪይቱ ኢትዮጵያ ያለው ሁኔታ ጤናማ ቤተስብ ለመመሥረት ያለው ዕድል አስተማማኝ ባይሆንም ÷ ተረካቢን ትውልድ ለማፍረት የተለያዩ ብሔራዊ ተቋማት የመመሥረት አስፈላጊነቱ ቀጣይና ዘለዓለማዊ ነው። ብሔራዊ ተቋማት ስንል በሀገር አቀፍ ደረጃ÷ ለመላዋ ኢትዮጵያና ዜጎቿ ሁሉ በእኩልነት ጥቅም የሚሰጡ ÷ ሀገራዊ ራዕይና ዓላማ ያላቸው ተቋማትን ማለታችን ነው ። እነርሱም ሃማኖታዊ ÷ ባህላዊ÷ እንዲሁም የትምህርት÷ የልማት÷ የመከላከያ÷ የመረጃ÷ የሳይንስና ቴክኒዮሎጂ÷ የኢኮኖሚና የፋይናንስ÷. ..ወዘተ ናቸው። ምኩራቦች÷ ገዳማትና አድባራት መስጊዶች ሁሉ የአንድ ሀገር ሃይማኖታዊ÷ ታሪካዊና ባኅላዊ ተቋማት ናቸው። እነኝህ ተቋማት ለብሔራዊ ጥቅምና ራዕይ እንዲጠቅሙ ሆነው ከተቋቋሙ ከተጠበቁ÷ ተረካቢውን ትውልድ ለማዘጋጀት የሚያስችላቸውን ተግባርና አደራ እዲሁም የሞራል ብቃትና ሥልጣን ሊኖራቸው ይችላል። ተረካቢው ትውልድም በበኩሉ ከነኝህ ተቋማት÷ የመንፈስ÷የመልካም ጠባይ ሰብዕና ÷ የሥነ-ሥርዓትና ግብረ-ገብ÷ የሀገር ፍቅር÷ የአካልና የአዕምሮ ዕድገት÷ የዕውቀት ብልፅግናን እየተመገበ ያድጋል። የሀገሩን ታሪክ÷ ባህልና ዕምነት መልክዓ ምድርና የአየር ጠባይ÷ አራዊትና እንስሳት አዕዋፋት ዕፅዋትና አዝርዕት የመሳሰሉትን ሊያውቅ የሚያስችሉት ብሔራዊ ተቋማት ይሆናሉ ። የእነኝህ ሁሉ የመጨረሻ ላዕላይ ተቋም የሚሆነው ደግሞ መንግሥት ነው ። መንግሥት የሚባለው ተቋም በበኩሉ በሕዝብ ዘንድ አመኔታም ሆነ አክብሮት ሊያተርፍ የሚችለው፤ ለሕዝብ ጥቅምና ለሀገር ህልውና ቆሞ ሲገኝ ነው ። ይህ ዓይነቱ መንግሥት ዕውን የሚሆነው ደግሞ የዴሞክራሲ ሥርዓት ሰፍኖ ሕዝብ በነፃ መንግሥቱን ሲመርጥ ብቻ ይሆናል ። መንግሥት የተሰኘው ተቋም የአንድ ሀገር ከፍተኛው ተቋም እንደመሆኑ ÷ በሀገሪቱ ውስጥ በሚቋቋሙት የተለያዩ ተቋማት ላይ ከፍተኛ ተፅዕኖ ይኖረዋል። በተለይ ደግሞ ዴሞክራሲያዊ መንግሥት መሆኑን በይዘትና በተግባር ካረጋገጠ÷ ተቋማቱ ሁሉ በነፃ ለመንቀሳቀስና ለማገልገል የሚኖራቸው ዕድል ሰፊ ይሆናል ። እነኝህ ልዩ ልዩ ብሔራዊ ተቋማት በበኩላቸው የወቅቱ ወጣት ትውልድ÷ የነገዋን ሀገር በብቃት ሊረከብ የሚያስችሉትን ዕውቀትና ዝግጅት ÷ ተመክሮና ሥልጠና ባኅርይና ሰብዕና እንዲያገኝ ያሰናዱታል። ነገ ሀገሪቱን ለመረከብ ብቃት ሊኖረው የሚገባውን ትውልድ የማዘጋጀት ኃላፊነት ሊወስዱ የሚችሉትና የሚገባቸው÷ቤተሰብ÷ኅብረተሰብ÷ተቋማትና መንግሥት ናቸው ። ሁሉም በየእርከናቸው ተረካቢውን ትውልድ የማሰናዳት ኃላፊነትና ግዴታያላቸው መሆናቸውን መረዳት ይኖርባቸዋል። የአንድን ሀገር ወጣት ትውልድ ለሚቀጥለው ዘመን ሳያዘጋጁ ቢያልፉት ጥለውት የሚሄዱት ሕዝብ÷ አስተማማኝ ነፃነት÷ አንድነቱና ውኅደቱየጠነከረ ዜጋ÷ዳር ድንበሩ የተከበረ ሀገር ማግኘት ያስቸግራል። ለዚህም ነው÷ ዛሬ የወያኔ መሪዎች÷ የቆዩትን የኢትዮጵያ ተቋማት እያጠፉ በራሳቸው አካልና አምሳል ፀረ ኢትዮጵያ ዋልጌ ተቋማትን በመፈልፈልፍ ላይ የሚገኙት ። ይህ ማለት እንግዲህ÷ ሀገርን እንደ ሀገር ሕዝብንም እንደ ሕዝብ እንዳይቀጥሉ መፍረድ ይሆናል ። በመሆኑም÷ሀገርን እያጠፉ ስለተተኪ ትውልድ ማሰብ የሚቻል አይሆንም ።

በአንድ ሀገር ውስጥ የሚገኙ ልዩ ልዩ ተቋማት፥ በፅኑ መሠረት ላይ መታነጻቸው ብቻ ሳይሆን፥ ተከብረውና ተጠብቀውም ሊኖሩ የግድ ይላል ። በየጊዜው የተፈራረቁት መንግሥታት እንደ ተቋምነታቸው በአቋቋሚቸው መሪዎች እየተዋረዱ፥ ሰብዕናቸውን እያረከሱ ተአማኒነታቸውንም እያጡ በመሄዳቸው በሕዝብ ዘንድ እየተናቁና እየተጠሉ ስለመጡ ከአቋቋሚቸው ግለሰቦችና ቡድኖች ጋር ደብዛቸው እየጠፋ ሄዷል። የፊውዲሉ ሥርዓት የራሱን መንግሥትና ተቋማት በማዋረዱ፥ ሕዝቡንም በመጥላቱ በመናቁና በመጨቆኑ፥ በሕዝቡ ዘንድ ተጠልቶና ተዋርዶ ወደ ማይቀርበት ጉድጓድ ገብቶ ቀረ። ከሥርዓቱ በኋላ ስለምትኖረው ሀገር አላሰበላትም። ተተኪ ትውልድ የሚባል ኃሳብ ሳይኖረው በመቅረቱም፥ ኢትዮጵያን ተረካቢ ትውልድ አልባ አድርጓት ሄደ። የደርግም ሥርዓት የዚህን ታሪክ ሂደት ተከትሎ ራሱ ያቋቋመውን መንግሥትና ተቋማት አዋርዶ ሀገር አጥፍቶ ጠፋ ። ተረካቢ ትውልድ የሚባል ቁም ነገር ለማሰብ ዓላማና ጊዜ ስለ አልነበረው ፥ ተረካቢ የሚሆነውን አንድ ትውልድ መትሮት በታሪክ ጉድፍ ተለውሶ ቀረ ። ሀገሪቱንም ለበላዒ-ሰብ -ለገንጣይ አስረከባት። ደርግ ጥሎለት የሄዳትን ሀገር በቀላሉ ያገኘው ወያኔ፥ ወትሮውንም ቢሆን አፈጣጠሩና ዕድገቱ ዓላማና ግቡ ለመላ ኢትዮጵያ ስለ አልነበረ ፥ አሁን የሚሰራውን ድርጊት ቢፈጽም አያስገርምም ። በመሆንም ለሚያጠፋው ሕዝብና ሀገር ፥ ተተኪ ኃይልና ተረካቢ ትውልድ እንዲኖርው ይጨነቃል ተብሎ አይጠበቅም ። ኢትዮጵያን እንዳልነበረች አድርጎ ከሚያጠፋ ብሔረተኛ ቡድን ተረካቢ ትውልድ ሊመጣ አይችልም ።ታዲያ፥በባጎርዩና በድርጊቱ በሕዝብ ዘንድ የተናቀ ፥የተጠላና የተዋረደ ማንኛውም ሥርዓትና ተቋማ ለሚቀጥለው ሀገርና ትውልድ የኋላ ልጅ ይጨነቅበት ቢል የሚያስገርም አይሆንም ። የኋላ ልጅ ይጨነቅበት የሚል አመለካከት ፥ከእኔ በኋላ ሰርዶ አይብቀል አለች ከተባለችው እንስሳ አባባል ፈጽሞ ሊለይ አይችልም።ተረካቢ ትውልድያልተዘጋጀላቸው ተቋማት ዛሬ ፥ በመኖርና ባለመኖር መካከል እየተጠራሞቱ ይገኛሉ።ታሪካዊቷ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተክርስቲያን ለዚህ አባባላችን ህያው ምስክር ነች።

በአፍሪካ አህጉር ብቻ ሳይሆን በሦስተኛው የዓለም ሀገሮችም ሳይቀር ዝናን አትርፎ የነበረው የአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ አሁን የወረደበትን ዝቅተኛ ደረጃ ለታዘበ ሰው፥ የሀገሪቱ ብሔራዊ የትምህርት ሁኔታ የቱን ያህል የተጎዳ ብቻ ሳይሆን የተማሪዎቹም በዘርና በጎጥ መከፋፈል የነገዋን ሀገር የሚረከብ ትውልድ ያለመኖሩንም አስደንጋጭ ሁኔታ ለማወቅ አያዳግተውም ። የአንድን ሀገር የወደፊት ሁለንተናዊ ዕድልና ህይወት ለመረከብ የሚችሉ ወጣቶችን ለማሰናዳትና ለማደራጀት የዚያች ሀገር የትምህርት ተቋማት የሚያበረክቱት ፀጋና የሚጫወጡትም ሚና ዓይነተኛ መሆኑ የሚያጠያይቅ አይደለም ። እንዲያውም በማንኛው ሀገር ከሚኖሩ ተቋማት መካከል ፥ የትምህርት ተቋማት የተተኪውን ትውልድ አካልና አዕምሮ በሁለንተናዊው መልኩ ለመቅረፅ እጅግ አስፈላጊዎች ናቸው ። በተለይም፥ የሀገሪቱን ማንነት የዜጎቿንም ብሔራዊ ጥቅም እንዲሁም የታሪክና የፍልስፍና መለያ የሚሆኖትን እሴቶች ለመፍጠርና ለማስፋፋት የሚጫወቱት ሚና በቀላሉ የሚታይ አይደለም። ምንም እንኳን የአፄው ሥርዓት እንደ ሥርዓቱ ብዙኃኑን የኢትዮጵያን ኅብረተሰብ ክፍሎች የጨቆነ ፥ የበደለና የረገጠ መሆኑ ባይዘነጋም፥ በጊዜው በነበሩት የሀገሪቱ የትምህርት ተቋማት፥በተለይም በወቅቱ ስመ ጥር

በነበረው የአዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ ውስጥ እየተማረ ያደገው ትውልድ ፥ የሕዝቧን መከራና ሮሮ ለመቅረፍ የተነሳው ለመላዋ ኢትዮጵያና ለዜጎቿ ፍትኅ ርትዕ፥ ለዴሞክራሲ ሥርዓትና ለሀገራዊ ልዕልና እንደነበር የታሪክ ማስረጃ ሊጠየቅበት የሚችል አይደለም ። ያትውልድ ለሚወዳት ሀገሩና ለሚያስብለት ሕዝብ የታገለለት፥ መፈክር በማንሳት ብቻ ሳይወስን ፥ የመጨረሻውን የህይወት መሥዋዕት በመክፈልም ጭምር ነበር ። ሁለቱም ተፈራራቂ ሥርዓቶች ያን የሀገር አለኝታ ተተኪ ትውልድ መተሩት ። ለዚህም ነው ዛሬ የኢትዮጵያ ሕዝብ፥ የተተኪ ትውልድን አስፈላጊነትና አንገብጋቢነት ከመቸውም ጊዜ በበለጠ የሚፈልገው። ለማየትም የሚጓጓው።

የሀገሪቱ ብሄራዊ ህገ መንግሥት ሊመነጭ የሚገባው በሀገሪቱ ዜጎች ፍላጎት፥ ተሳትፎና ፈቃድ መሆን ስለአለበት ከከፍተኛ የትምህርት ተቋማት የሚቀሰሙ ትምህርቶች የሀገሪቱን የታሪክ፥ የፍልስፍና፥ የዕምነት፥ የባኅል እንዲሁም የሕዝቡንም ጠባይና ራዕይ ያገናዘቡ ሊሆኑ ይገባል። በዚህ የትምህርት አሰጣጥና ፍልስፍና ላይ የተመሠረተ ሥርዓተ ትምህርት ሂደት የተመሩ የሀገሪቱ ወጣቶች፥ የነገዋን ኢትዮጵያ ለመረከብ ዝግጅትና ብቃት ሊኖራቸው ይችላል ተብሎ ይታመናል ። ከጎጥና ከመንደር ባሻገር ለመላዋ ኢትዮጵያ ብሔራዊ ጥቅምና ለህዝቧም ራዕይ የሚያስብ ትውልድ ዛሬ ከማንኛው የዓለም ሀገሮች በበለጠ ሊኖራት የሚያስፈልጋት ሀገራችን ኢትዮጵያ ነች ብለን እናምናለን ። ይህ ዕምነታችን የተመሠረተው ፥ በቅድመ የካቲት አብዮት የነበረውን ትውልድ ሀገራዊ ፍቅርና የጀግንነት ታሪክ እንዲሁም ፥ የሀገሩንና የወገኑን ፍቅር ለመግለጽ ሲባል የከፈለውን መሥዋዕት ማጠየቂያ በማድረግ ነው ። በሀገራችን የቆዳ ስፋት፥ የብሔሮች ስብጥር፥ የዜጎቿም ባኅሎች፥ ቋንቋዎች ብሎም የአምልኮትና የዕምነቶች ምክንያት፥ በግድ ሀገራችን የፌዴራል ሥርዓት እንደሚያስፈልጋት የሁሉም ዜጋ ፍላጎትና ዕምነት ነው ። ይህም ሥርዓት ለአስተዳደሩ ቅልጥፍና ለዳኝነቱ ተግባር ፍትኃዊነት፥ለልማቱ እንቅስቃሴ ርምጃ የሚበጅ ይሆናል። ይህ ሁሉ ዕውን ሊሆን የሚችለው ግን፥ የዴሞክራሲያዊ ሥርዓት ተመስርቶ በተግባር ሲውል ይሆናል። ታዲያ ከላይ በተዘረዘሩት የሀገሪቱ ዕውነታዎች ምክንያት ፌዴራላዊ ሥርዓት አማራጭ የሌለው ቢሆንም ተተኪውን ትውልድ ለማዘጋጀት ሲባል ግን ሁሉንም የሀገሪቱ ህፃናት ሊያገናኛቸውና ሊያዋኅዳቸው የሚችል አንድ ብሔራዊ ሥርዓተ ትምህርት መኖሩ፥የሀገሪቱን የማይገሰስ-የማይደፈር ሉዓላዊነትና የሕዝቧንም አንድነት የሚፈልግ ዜጋ ሁሉ ይስማማበታል። ወያኔዎቹና ሌሎች እንደነርሱ ጠባብ አመለካከት ያላቸው ክፍሎች፥በኢትዮጵያ ሕዝብ አንድነትና በሀገሪቱም ሉዓላዊነት ደንታ ስለሌላቸው፥ ምናልባት ይህ ሃሳብ ላይጥማቸው ይችላል። ለኢሕአፓ ግን መሠረታዊ ነው። ይህም በመሆኑ፥ ስለታላቋ ኢትዮጵያ በመታገሉና በመሰዋቱ እነኝህ ጠባቦች ፓርቲውን "ዓባይ ኢትዮጵያ" በሚል ስያሜ ጠርተውታል። እነርሱ ይህንን አቋሙን እንደ ስድብና ውርደት ቢቆጥሩትም፥ ለኢሕአፓ አባላት ግን፥ ታላቅ ኢትዮጵያ መባል ፥አኩሪ ታሪካቸውና የዜግነት መለያቸው ሆኗል ። ለዚህም ነው የተረከቧትን ሀገር ለተተኪው ትውልድ ማስረከብ መሠረታዊ ዕምነታቸው ብቻ ሳይሆን የትግላቸው ዓይነተኛ ግብም ጭምር የሚሆነው። በታላቋ ኢትዮጵያ ዘለዓለማዊነት ያላቸው አቋም፥ ጊዜ የማይሽረው፥ መከራ የማይለውጠው በመሆኑም የኢትዮጵያ ቋሚ ጠላት መሆኑን በተግባር ያስመሰከረው ወያኔ ፥

በኢሕአፓ አባላት አስከሬን ላይ ተረማምዶ አዲስ አበባ ለመግባት በቅቷል:: እዚህ ላይ ሁሉም ኢትዮጵያዊ ዜጋ ፈፅሞ ሊዘነጋው የማይገባ አንድ የታሪክ ሐቅ ቢኖር ፥ የደርግ ባለሥልጣናት ያን የመሰለ የኢትዮጵያ የመከላከያ ሠራዊት ያለ ሁነኛ መሪ አውላላ ሜዳ በትነውት በሚሸሹበት ወቅት፥ የኢሕአፓ ሠራዊት ግን ከወያኔ ሠራዊት ጋር አንገት ለአንገት ተያይዞ ይዋደቅ የነበረ መሆኑን ነው:: ለዚህም ነው ደርግ ትላንት ለወያኔ ያስረከባትን ሀገር፥ ጠፍታ ከመጥፋቷ በፊት ተረካቢ ትውልድ ከወዲሁ ሊዘጋጅ ይገባዋል ብሎ ኢሕአፓ በፅናት የሚታገለው::

አንድ ሕዝብ ብልህነቱንና፥ ታላቅነቱን የሚያስመሰክርበትና በታሪክም ፍርድ ትክክለኛ ብያኔ ሊያስገኙለት ከሚችሉት መሠረታዊ ሚዛኖች መካከል፥ የነገዋ ሀገር ዕድል ምን ሊሆን ይችላል? እኛ ካለፍን በኋላስ ይህችን ሀገር ምን ዓይነት ትውልድ ሊረከባት ይችላል? የሚረከባትን ሀገር ተረክቦ ኃላፊነቱን የሚወጣ ትውልድ እየተዘጋጀ ነውን? ...ወዘተ ጥያቄዎችን ጠይቆ አዎንታዊ መልስ የማግኘት ችሎታውን ሲያረጋግጥ ነው:: በዛሬይቱ ኢትዮጵያ ይህ ሁኔታ ይፈጸማል ብሎ ማለት ቀርቶ መታሰቡ እንኳን የመነመነ ነው:: የአሁኗን ሀገር ለም መሬቶችን ለውጭ ዜጎች በሃራጅ በመቸብቸብ ያለ አጥፊ ዘረኛ ቡድን፥ የዓለም አቀፍ ድንበሯንና ወሰኗን ያስደፈረ ወያኔ፥ ብሔራዊ ልዕልናዋንና ፖለቲካ ነጻነቷን ለውጭ ባዕዳን ያስገዛ ህሞተ ቢስ ቡድን፥ ለነገይቷ ኢትዮጵያ እጣ ፋንታ ያስባል፥ ይቆረቆራል ብሎ የሚያስብ ዜጋ በአሁኑ ስዓት ፈልጎ ማግኘት አይቻልም:: ይህንንም እራሱ ወያኔም ቢሆን አይስተውም :: በመቸውም የታሪክ አጋጣሚና በየትኛውም ሁኔታ ወደ ሥልጣን ኮርቻ የወጣ አምባገነናዊ አገዛዝ የሚያራምድ ቡድን፥ ሌላው ቢቀር ፥ቢያንስ ቢያንስ ስለሀገሩ ነጻነትና ለሕዝቡ ክብር ቀናዒ እንደሚሆን የአያሌ አምባገነን ሥርዓት አራማጆችን ታሪክ መጥቀስ ይቻላል:: አምባገነኖች፥ የሥልጣን ጥማቸውን ለማርካት ፥ ዲሞክራሲን ለማጥፋት ብቻ ሳይሆን ፥ የሥልጣን ተቀናቃኞቻቸውንም ለመፍጀት ሲሉ አረመኔዎች ይሆናሉ:: የፖለቲካ ተቃዋሚዎቻቸውን፥ የሰብዓዊ መብት ተከራካሪዎችና የኀሊና እስረኞችንም ወኅኒ በመወርወር ለዘመናት ሊያሰቃዩ የሚችሉበት ሁኔታም መኖሩን የዓለም ታሪክ መዝግቦታል :: አሁንም ይህ ድርጊት በመፈፀም ላይ መሆኑ በገሀድ የሚታይ ክስተት ነው:: ነገር ግን ሁሉም ባይሆኑ ፥ አንዳንድ አምባገነኖች ፥ ሌላው ቢቀር እንኳ ፥ ለሀገራቸው ብሔራዊ ነፃነትና የግዛት ልዕልና፥ ለዜጎቻቸውም አንድነትና ዕድገት፥ በመሰላቸው መንገድ ቀናዒ እንደነበሩ የታሪክ መዛግብት ይመሰክራሉ:: ይህ ግን ለዴሞክራሲ ለነፃነትና ለሰብዓዊ መብት ያስባሉ ወይም ይጨነቃሉ ማለት አይደለም :: ብሔራዊ ስሜታቸው ግን በአንፃራዊ ግምጋሜና በበርካታ ገፅታው ሲመዘን የሚያስኮንናቸው አይሆንም:: ምናልባት ሀገር ማስፋፋት ይከጅሉ እንደሁ እንጅ፥ አብሶማ የራሳቸውን ሀገር ቆርሶ በመስጠትና ለም መሬቶቹንም ለባዕዳን በመቸብቸብ የሚጠረጠሩ አይደሉም :: ይህን ግን በዘመናዊቷ የኢትዮጵያ አሳፋሪ ታሪክ በመፈፀም ክብረ-ወሰን ያስመዘገበው የወያኔ ሥርዓት ያለህፍረት የሚናገረው ሆኗል :: በጣም የሚገርመውና የሚያሳዝነው ግን ፥ የወያኔ መሪዎች ይህን ሁሉ ብሔራዊ ወንጀል በመፈጸም ላይ የሚገኙት ፥ የኢትዮጵያን ሕዝብ በመናቅና በማዋረድ ብቻ ሳይሆን ፥ በታሪክና በሕግ ፊት ተጠያቂነት ለመጨነቅ ደንታ ቢስ በመሆናቸውም ጭምር ነው:: እንዲህ ዓይነት ሰብዕና ካለው ስብስብ

የሚወረስ ለሀገር የሚጠቅም መልካም ቅርስ ይገኛል ብሎ የኢትዮጵያ ሕዝብ ማሰብ ቀርቶ ምኞትም የለውም:: ከዚህ መሠረታዊ ግንዛቤ በመነሳት ትላንት የተፈራረቁት ሥርዓቶችም ይሁኑ ከእነርሱ በኋላ የመጣው ወያኔ ለሀገርና ለሕዝብ እንደልሆኑና እንደማይሆኑ ስለሚረዳ ለራሱ የሚጠቅመውን ውሳኔ ከመውሰድ በቀር ሌላ አማራጭ ሊኖራው አይችልም:: ተተኪውን ትውልድ ለማዘጋጀት የቀጥታ ኃላፊነቱ የኢትዮጵያ ሕዝብ ሆኖ፥ ለዚህ ዓላማና ፍላጎት ችሎታና የሞራል ብቃት ያላቸው ተቋማት ትብብርና ዘላቂ ግዴታ ታክሎበት የሚፈጸም ብሔራዊ ተግባር ነው:: መንግሥታትና ሥርዓታቸው የሚለዋወጡ እንደመሆናቸው፥ የሀገርን ጥቅም በዘላቂ መልኩ ሊጠብቁና ሊያስጠብቁ የሚችሉት የሕግና የሞራል ግዴታ ያላቸው ቋሚ ተቋማት ናቸው:: ተተኪ ትውልድ የሚወጣው በረጅም የሕዝብና የተቋማት ያልተቋረጠ ጥረትና ሂደት እንደመሆኑ፥ በአንድ ዘመን በሚኖር ሕዝብ ጥረትና ድካም የሚወሰን አይሆንም ። የአንድ ሀገር ሕዝብ ሥነ-አዕምሮ ፥ የአኗኗር ጠባይና መስተጋብርን፥ ያካተተና የወቅቱንም ሁኔታና የወደፊት ራዕይና ተስፋ እያገናዘበ፥ በአስተማማኝ መረጃና በሰላ ትንታኔ ላይ ተመርኩዞ የሚወጣ ፖሊሲና የሚወስደው እርምጃ ፥ ለዚያ ሀገር ጥቅም ዋስትና ይኖረዋል ። የተተኪው ትውልድም ዕጣ ፋንታ በዚህ ውስጥ ተካታች ይሆናል::

ዛሬ በሀገራችን ልክ እንደ ፖለቲካው፥ ኢኮኖሚው፥ ማኅበራዊ ኑሮውና ሌሎቹም ብሔራዊ ችግሮች ውጥንቅጣቸው እንደወጣ ሁሉ፥ የኢትዮጵያ ወጣት ትውልድ ዕድልም ከዚህ በባሰ እንጅ በተሻለ ሁኔታ ላይ አይደለም:: በምርምር ለይ የተመሰረተ አሀዝ ለመጥቀስ ለጊዜው ባይቻልም ፥ቁጥሩ የሚያስደነግጥ ብዛት ያለው የሀገሪቱ ወጣት ትውልድ፥ የጫትና የሌሎች አደንዛዥ ዕፆች ሱሰኛ ሆኗል:: በትምህርቱ ፖሊሲ ከንቱነት የተነሳ አብዛኛው ወጣት ከትምህርት ገበታው እየተፈናቀለ፥ ሥራ ፈትና አውታታ ሆኗል:: ሥራ የፈታ የወጣት አዕምሮ ደግሞ ለልዩ ልዩ በሽታ፥ ድርጊትና ወንጀሎች እንደሚጋለጥ ለመረዳት የማኅበራዊ ጠበብት መሆንን አይጠይቅም:: ሥራ- ፈት ወጣት፥ እህል-ፈጅ እንጅ አምራች ሊሆን አይችልም ። አምራች ዜጋ የሌላት ሀገር ደግሞ ዝንት-ዓለሟን ከድህነት ትላቀቃለች ብሎ ማሰብ ዘበት ነው ። ታዲያ የሀገራችን ወጣት ትውልድ፥ እንኳንስ እኛ የምንመኝለትን የነገዋን ኢትዮጵያ የመረከብ ኃላፊነት ለመቀበል የሚስችለውን ዝግጅትና ትምሕርት ማግኘቱ ቀርቶ፥ ጤናማ አዕምሮና አካል እያገኘ ለማደግም ቢሆን የሚያስችለው አካባቢ አልተፈጠረለትም:: ዛሬ ፥ የነገዋን ኢትዮጵያ ሊገነባት የሚችል ተተኪ ትውልድ እያደገ አይደለም ። ዛሬ ያልተዘራ፥ ያልበቀለና ያልተኮተከተ ቡቃያ ነገ ምርት ሊሆን አይችልም ። ይህም በመሆኑ ፥ ሀገራችን ኢትዮጵያ ተተኪውን ትውልድ አስመልክቶ፥ ነገ-ተነገ ወዲያ አዝመራ ኖሯት ፍሬ መልቀም አትችልም::

ኢሕአፓ የተተኪውን ትውልድ አስፈላጊነት የሚያየው፥ ከወያኔ መውደቅ-አለ መውደቅ አኳያ አይደለም:: ጨቋኝ ሥርዓት፥ በሕዝብ የተጠላና የተተፋ በመሆኑ፥ ወያኔ እስከ ዘረኛ ሥርዓቱ ከእርሱ በፊት እንደነበሩት ሥርዓቶች ወደ ከርሰ-መቀብሩ እንደሚገባ ብዥታ አይኖረውም:: የኢሕአፓ የቅድሚያ የትግል ዕቅድ፥ ይህን ዘረኛ ሥርዓት ማስወገድ ቢሆንም፥ የነገዋን ሀገር

የሚቀበላት ተተኪ ትውልድ ዛሬ ማዘጋጀት ደግሞ ከትግሉ ሂደት ጋር እጅና ጓንት ሆኖ መሄድ እንዳለበት ያምናል፡፡ ተረካቢ ትውልድ ሲባል ለአንድ ሀገር ሁለንተናዊ አገልግሎት ሊያበረክት የሚያስችለውን ብቃትና ችሎታ፥ ባሕርይና ምግባር አሟልቶ የሚገኝ ትውልድ ማፍራት ማለት ነው፡፡ የነገው/ ዋ ኢትዮጵያዊ / ዊት ትውልድ ኢትዮጵያዊ ሰብዕናውን ሊመሠርትበት የሚያስችለው የማንነት መለያውን አምኖ ተቀብሎ በተግባር መግለጽ ይኖርበታል ፡፡ ይህ ምን ማለት ነው? ልክ እንደማንኛቸውም የዓለም ሕዝቦች ፥ ኢትዮጵያም የራሷን ማንነት የምት- ገልጽባቸው መለያዎች አሏት ፡፡ እነኝህን የማንነት መግለጫዎች መኩሪያዎቹና የህይወቱ ዋስተናዎቹ ናቸው ማለት ነው፡፡ እንደ ዜግነት እየቀጠለ ለመኖር ከፈለገ ፥ እነርሱኑ ተቀብሎና አክብሮ ሊይዛቸው ግድ ይላል ፡፡ ከሁሉ በላይ የኢትዮጵያን ሕዝብ እኩልነትና አንድነት አምኖ መቀበል የህልውናው መሠረት ነው ፡፡ በዜጎቿ እኩልነት ላይ የተመሠረተ የኢትዮጵያ አንድነት፤ የዜጎቿ ሁሉ በነፃነት የመኖርያ ለመኖር ጥያቄን ያመጣበታል ፡፡ የኢትዮጵያን የመኖር ጥያቄ በማያሻማ መልኩ በመመለስ ዘለዓለማዊቷ ኢትዮጵያን ቀጣይ ሀገር እንድትሆን ማድረግ የተተኪው ትውልድ ግዴታና ተልዕኮ መሆኑን አምኖ መቀበል ብቻ ሳይሆን ለዚህ ከባድ ተልዕኮ በቂ ዝግጅት ማድረግ እንዳለበት ያልተረዳ ትውልድ፥ ሀገሩን ለውጭና ለውስጥ ጠላቶቿ አሳልፎ እንደ መስጠት ይቆጠራል ፡፡ ደርግ ይህንኑ ነበር የፈፀመው፡፡ ያ ብሔራዊ ጉዳትና ውርደት በሌላ መልኩ እንዳይቀጥል ከተፈለገ ፥ ከጎልፈተ-ወያኔ በኋላ ለምትመጣው ሀገር ከአሁኑ ማሰብ ይገባል ፡፡

በእኛ ዕምነት፥ መጭው ትውልድ ከእርሱ በፊት ከነበረው ትውልድ ሊወርሳቸው የሚገባው መሠረታዊ ነገሮች አሉ እንላለን፡፡ ከሁሉ በፊት የሀገሩን ነፃነትና ሉዓላዊነት የሕዝቡንም መብትና አንድነት የሚፈታተኑትን ማንኛቸውንም የውጭ ኃይሎች በመቋቋም የሀገሩን ህልውና ማስከበር ከቀደምት ትውልድ ያገኘው ውርስ ነው ፡፡ የሀገር ውስጥ አምባገነን ጨቋኞችን መታገል፥ ዴሞክራሲ ሥርዓትና ለፍትሕ-ርትዕ መቆም የትላንቱ ትውልድ አንፀባራቂ ታሪክ መሆኑን በኩራት ሊያምንበት ይገባል ፡፡ አይበገሬነት ፥ የሕዝብ ወገንተኝነት ፥ የሀገር ተቆርቋሪነት ፥ ለብሔራዊ ዓላማ መስዋዕትነት፥ የሀገርን ታሪክ፥ የሕዝቧንም ባህልና ዕምነት ማክበርን የአንድ ትውልድ የተለየ ፀጋ መሆኑን ማመን ይገባዋል፡፡ ከዚህም ሌላ፥ ሀገሩን ከኋላ ቀርነት፥ ከበሽታ፥ ከረሀብና ቸነፈር፥ ከድንቁርናና ከድህነት ነፃ ለማውጣት ግንባር ቀደም ሚና የሚጫወተው ትኩሱ ኃይል እንደሆነ በትክክል ሊገነዘበው የግድ ይላል ፡፡ ከዚህም በቀር፥ የሀገሩን የፖለቲካ የኢኮኖሚና የማህበራዊ ኑሮ ተጨባጭ ሁኔታዎችን በማገናዘብ ፥ በሀገር ልማትና ግንባታ የመሳተፍ ግዴታውም መብቱም መሆኑን መርሳት የለበትም ፡፡ በሃያ አንደኛው ምዕተ-ዓመት ያለቸው ኢትዮጵያ በማንኛውም መስፈርት ብትመዘን ሲበዛ ወደኋላ የቀረች ሀገር መሆኗን ተረድቶ ፥ በሳይንስ ፥ በቴክኒዮሎጅ ፥ በዕደ-ጥበብ እና በአጠቃላይ በዘመናዊ ውቀት ራሱን ያሳደገና፥ የኢትዮጵያን የፖለቲካ የኢኮኖሚና የሳይንስ መልክዐ-ምድር የመለወጥ ኃላፊነት የራሱ ድርሻ መሆኑን የተገነዘበ ወጣት ትውልድ ሊሆን ይገባዋል ፡፡ ራስን ከአልባሌ ጠባይና በሕዝብ ፊት ከሚያዋርድ ፥ በታሪክም ከሚያሳፍር ተግባር ማግለል ፥ የአንድ ሀገር ወጣት ዓይነተኛ ባኅርዩ መሆኑን የተረዳ ትውልድ ፥ የዚያ ሀገር ቅርስ መሆኑን ማወቅ ብልኅነት ብቻ

ሳይሆን፥ በሕዝብ ፊት ተመስጋኝ ይሆናል ። ከዚህም በቀር፥ የሞራልና የመንፈስ ጥንካሬውን ከአካል ማጎልመስ ጋር ያዋኻደ ትውልድ ለሀገሩ ነፃነት ዋስትና ብቻ ሳይሆን፥ ብሔራዊ ሀብትም ጭምር ነው ። ሙስና፥ ዕበላ-ባይነት፤ አድላዊነትና ለግል ዝና ሲባል ብኩርናን ለጭብጥ ምስር መለወጥ፥ የሰውን ልጅ ክብር ከሚያዋርዱ ባኅርያት መካከል ዋና ዋና መሆናቸውን እየተረዳ ያደገ ትውልድ ሕዝቡን ለማገልገል የሞራልና የሥነ አዕምሮ ብቃትና መሰናዶ አለው ማለት ይቻላል ። በጠቅላላው አነጋገር ሁለንተናዊውን መስፈርት አሟልቶ የተገኘ ትውልድ ዛሬ ኢትዮጵያን ከወደቀችበት የዘረኞች አምባገነን ሥርዓት ለማውጣት በሚደረገው ትግል ዓይነተኛ ሚና ከመጫወቱም አልፎ-ተርፎ የነገዋን ኢትዮጵያ በዴሞክራሲ ፥ በሳይንስና በቴክኒዮሎጂ ለማሳደግ በሚደረገው ሀገር አቀፍ ግንባታ ግንባር ቀደም ድርሻ ይኖረዋል።

ይህንን ዘረኛ አምባገነን ቡድን ለማስወገድ በምናደርገው የሞት-ሽረት ትግል ውስጥ፥ የጎሊና ዕረፍት ከሚነሱን መሠረታዊ ጥያቄዎች መካከል፥ የነገዋን ኢትዮጵያ ዕድል ለመወሰን ምን እየተደረገ ነው? የሚለው የመጀመሪያውን ቦታ ይዟል። ለዚህ መሠረታዊ ጥያቄ ዋስትና ያለው አስተማማኝ መልስ መግኘት ለኛ ወሳኝነት አለው። በእኛ ዕድሜ ሦስት የተለያዩ ርዕዮት፥ይዘትና ዓላማ ያላቸው ሥርዓቶች ተፈራርቀዋል ። ሁለቱ እንደ ወያኔ ኢትዮጵያን ለማጥፋት ዓላማ ብለው ያልተነሱም ቢሆኑም ፥ በድርጊትና በሂደት ኢትዮጵያን ለማዳን አልተቻላቸውም ። ተተኪውን ትውልድ ለማዳን በሚመለከት የረባ ተግባር አልፈፀሙም። አብሶማ ደርግ እያወቀው በጭካኔ ሳያውቀው በድፍረት ተተኪውን ትውልድ መትሮት ሄደ። በተገነባው ላይ መሥራት ሲገባው፥ የነበረውን እንዳልነበር ማድረግ ብቻ ሳይሆን ያልነበረን ለማምጣት ብሎ ሁሉንም አጠፋፍቶት ወደቀ። መተኪያ ሳይዘጋጅ ታለፈ።ተረካቢ ትውልድ ጠፋ። በደርግ ዘመን የነበሩት አስራ ሰባት የትግል ዓመታት፥ ከፍተኛ የሕይወት መሥዋዕት ቢጠይቁም ፥ ከደርግ በኋላ ምን ይመጣል የሚለው ቁም ነገር ተገቢውን አጽንዖት ሳያገኝ ቀረ ። የገባውን የትግል ቃል-ኪዳን ጠብቆ ትግሉን የቀጠለው ኃይል / ትውልድ ፥ አጥፍቶ የሚሸሸውን ሲያባርር ፥ ለማጥፋት የሚመጣውን ሲከላከል፥ የሁለቱ ሀገር አጥፊዎች ሰለባ ሆኖ ተጎዳ። አይከፍሉ መስዋዕት ከፈለ። የወያኔ ቡድን ከእርሱ በፊት ከነበሩት ሁለት ሥርዓቶች በመሠረታዊ መልኩ የሚለየው ፥ ይህ ዘረኛ ቡድ ከጥንስሱ ጀምሮ እስከ ዛሬ ድረስ ኢትዮጵያን ለማጥፋት ይዞት የተነሳውን ዓላማ በተግባር እየተረጎመ የቀጠለ መሆኑ ነው ። ከጎልፈተ ወያኔ በኋላ የኢትዮጵያ ዕድል ምን ሊገጥመው ይችላል ? ለሚለው ጥያቄ መልስ መፈለጉ ቀርቶ ፥ ጥያቄውን እንኳን የሚያነሱት ስንቶቹ እንደሆኑ ሁሉም የራሱን ህሊና ይፈትሽ ። እኛ ግን የኢትዮጵያ ጉዳይ የኋላ ልጅ ይጨነቅበት ብለን ለመጪው ትውልድ የምንለጋው ሀኬት አይደለምና የታሪክና የትውልድ ተወቃሾች መሆንን አንሻም። የቆምንበት የትግል ዓላማም ይህንን ለማሰብ አይፈቅድልንም። በመሆኑም ተተኪውን ትውልድ ማዘጋጀትና ወያኔን ማንበርከክ ጎን ለጎን ማስኬድ የትግላችን ዓላማ ነውና ወጣት ኢትዮጵያውያንን ለትግል እንጠራለን፤ እናደራጃለን።

ወጣቱ ትውልድ ሀገሩን ለማዳን ለትግል በአንድነት ይነሳ!!